ብዕረኛው!
ከዓሣዬ
04/22/2010

የፋሺስት ባለሟል የኢሰፓው ኣውራ
ንስሃን የማያውቅ ሃይሉ ኣርአያ፣
እሱ ብሎ ምሁር የታሪክ ሥላቂ
ዛሬም እንደ ትላንት፣
ታጋዩን ኮንኖ ገዳዩን ኣድናቂ
በደም የጨቀዩ ታሪኩን ናፋቂ!።

ታድያ፣
እኔ ምን ቸገረኝ ብዕረኞች ካሉልኝ
እያወራረዱ ሃይሉን ሲያቅሙልኝ
የሣልቫጅ ምሁራንን ጣቱን ሲቆምጡልኝ
ፊልም ቀራጭ ባንዳውን ሲያኮማትሩልኝ
መቸሥ ምን እላለሁ፣
በፈረንጁ ቋንቋ በአማርኛው ሥንኝ
ብዕራችሁን ይባርከው! እናንተን ያኑርልኝ!።

የባንዳ ዲቃላን ኣረሞ ነቅላችሁ
የታሪክ በራዡን ባፍ ጢሙ ደፍታችሁ፣
ላንድ ኣፍታ እንኳን ቢሆን ፋታ ሣትሰጡት
ዳግም ላይነሣ እንጦርጦሥ ሥደዱት!።

ያባታችሁን ጋሻ ጦራችሁን ሰብቃችሁ
ፋሺስት ዘረኛውን ከትቢያ ቀላቅላችሁ
በኢትዮጵያዊው ቀለም በብዕራችሁ ደምቃችሁ
ዛሬም እንደ ጥንቱ እንደ ሰማዕቶቹ
ለሃገር ዘብ ቁሙ!
ለዓላማ ቁማችሁ፣በቃልኪዳን ጸንታችሁ!።

EthioLion.Com